በ
ለ
ጠ



አ
ም
ሃ

# ኢትዮጵያ

ጥቅምት 2005 | ፩ኛ ዓመት ቁጥር ፬ | በነጻ የሚሰራጭ

ተወርዋሪው

ጌ
ታ
ቸ
ው



ጥ
ሩ
ነ
ህ

የኢሕአፓ ታጋይ

ገጽ 5

የኢሕአፓን ታሪክ
መጻፍ የሚችለው
ኢሕአፓ ነው

ገጽ 6

ድርጅት ስንል መደራጀት
ሕብረት ስንል መተባበር

ገጽ 4



ምን...ይሰማ አገር?

ገጽ 3

## ዜና ዘገባ

## በወያኔ እና በሙስሊሙ መካከል ውጥረቱ አይሏል፡፡

## "መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሙስሊሙ ጎን መቆም አለበት"

ወያኔ፣ ሙሲልሙ ማህበረሰብ አል አባሽ የተሰኘ መጤ ሀይማኖት በሀይል እንዲቀበል ለማድረግ እየወሰደ ያለው የጉልበት ድርጊት፣ ከሙስሊሙ ማህበረሰብ በኩል ከፍተኛ የሆነ ተቃውሞ እንደገጠመው የሚታወቅ ሲሆን፣ በአሁኑ ሰዓት ሁኔታው እየከረረ መጥቶ በመጨረሻ ሰላማዊ የነበረው የሙስሊሙ ጥያቄ በወያኔ ማንአለብኝነት ምክንያት ወደ ከፍተኛ ቀውስ ሊለወጥ እየተቃረበ መሆኑን ከሰሞኑ ሁኔታ ለመረዳት ይቻላል፡፡

በቅርቡ በደቡብ ወሎ ቃሉ ወረዳ ውስጥ በወያኔ ታጣቂዎች እና በሙስሊሙ አማኝ መካከል በተፈጠረ ግብ ግብ 4 ሰዎች ከመገደላቸውም በተጨማሪ በደርዘን የሚቆጠሩ ሰላማዊ ሙሰሊሞች ይሰግዱበት ከነበረው መስጊድ ደጃፍ በፌደራል ፖሊሶች በጥይት ተደብድበው ከቆሰሉ በኋላ ወደ ሆስፒታል ተወስደዋል፡፡እንዲሁም ከፌደራል ፖሊሶች መካከል ሁለቱ መገደላቸውን በስፈራው ከነበሩ ያይን እማኞች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

እንደነዚህ የዐይን እማኞች ከሆነ፣በዕለቱ በወያኔ የፌደራል ፖሊሶች እና በሙስሊሙ ማህበረሰብ መካከል ከተፈጠረው ግብግብ በኋላ፣በርካታ ሙስሊም ወገኖች ወደ ጫካ መግባታቸው ይነገራል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው፣ሙስሊሙ ኢትዮጵያዊ ያቀረበውን የሙብት ጥያቄ ወያኔ በሀይል ለመጨፍለቅ መሞከሩን ከቀጠለ፣ሙብቱን ለማስከበር ሲል ጠመንጃ ማንሳቱ የማይቀር መሆኑን አመላካች ሲሆን፣ ይህም ሁኔታ ባገሪቱ ከፍተኛ የደም መፋሰስ ሊያስከትል እንደሚችል ብዙ ወገኖች ይገምታሉ፡፡

ከጅምሩም ቢሆን፣ወያኔ በሙስሊሙ ማህበረሰብ የሀይማኖት ጉዳይ ጣልቃ በገባ ማግስት ጀምሮ፣ ምዕመናኑ በሰላማዊና በኢትዮጵያዊ ጨዋነት ሁኔታውን ለመቃወም ሞክረዋል፡፡ ይሁንና ወያኔ ተቃውሞውን እንደተለመደው በሀይል ከመጨፍለቅ ባለፈ የወሰደው አንዳችም በጎ እርምጃ አልነበረም፡፡ ሙስሊሙ ማህበረሰብ በተጨማሪም ሁኔታው እየተባባሰ ሲሄድ፣ችግሩን ለመፍታት የመፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ በማቋቋም ተወካዮቹን መርጦ ከወያኔ ጋር ለመደራደር ሙከራውን ቀጥሎ ነበር፡፡ ይሁን እና አሁንም ወያኔ የሰጠው ምላሽ እነዚህኑ የመፍትሄ አፋላላጊ ኮሚቴ ተመራጮችን እስር ቤት ከቶ ማሰቃየት ነው፡፡ ይሁን እንጅ ሙስሊሙ ወገን፣ወያኔ የትግል ስሜቱን ለመስበር የቱንም ያህል ቢንቀሳቀስም፣ ሁኔታውን ትእግስት በተሞላበት መንፈስ እስከ መጨረሻው በሰላማዊ መንገድ ተቃውሞን በመቀጠል አይበገሬነቱን ማስምስከሩ አልቀረም፡፡ከጥቂት ሳምንት በፊት ወያኔ የመጅሊስ ምርጫ በሚል በመላው አገሪቱ የሙስሊሙን የሀይማኖት ተወካዮች ራሱ ባስመረጠ ማግስት፣ ሙስሊሙ ትእግስቱ የተሟጠጠ በመሆኑ ለወያኔ ቢጫ የማስጠንቀቂያ ካርድ አደባባይ ይዘው በመውጣት ካሳዩት በኋላ፣ ከዚህ በመቀጠል ቀይ ካርድ ነው የምንመዘው፣ቀይ ካርድ ደግሞ አደጋ አለው በማለት ግልጽ የሆነ መልዕክት ማስተላለፋቸው አይዘነጋም፡፡ አሁን በደቡብ ወሎ ውስጥ በወያኔ እና በሙስሊሙ መካከል የተደረገው ግብ ግብ ይሄው ቀይ ካርድ የተመዘዘ ለመሆኑ ግልጽ ምልክት መሆኑን ብዙ ወገኖች ያምኑበታል፡፡

ወያኔ፣ለማስመሰል ያህል መንግሥት በሀይማኖት ጣልቃ አይገባም እያለ ሕዝብን እና በተለይ ደግሞ ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ለማጭበርበር ይሞክር እንጂ፣አሁን በተግባር በሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይ እየፈጸመ ያለው ድርጊት ግን በሀይማኖት ጣልቃ ከመግባት ባለፈ የሙስሊሙን ማህበረሰብ ህልውና የሚፈታተን አደገኛ የሆነ ተግባር መሆኑን ሁኔታውን በቅርብ የሚከታተሉ ወገኖች ይናገራሉ፡፡ በመሆኑም ይላሉ እነዚህ ወገኖች፣" በመሆኑም አንድ ሰው ሀይማኖቱን በሀይል ኢንዲለውጥ ከተደረገ፣ ህልውናው አለ ለማለት አይቻልም በዚህ በ 21ኛው ክፍለዘመን በዙ ሚሊዮን ሙስሊሞችን በሀይል ሀይማኖታቸውን ቀይረው በሰላም ይቀመጣሉ ብሎ መገመት በራሱ ጤነኛ ከሆነ አእምሮ የሚመነጭ ሀሳብ አይደለም" በማለት አሁን በተጨባጭ የለውን ሀኔታ አስከፊ የሚያደርገው ይኸው እውነታ መሆኑን ይግልጻሉ፡፡ በመጨረሻም፣ ቀሪው ያኢትዮጵያ ሕዝብ ከሙሰሊሙ ወገኖቹ ጋር አብሮ ቢጋራ መቆም አለበት ብላችሁ ታምናላችሁ ወይ? በማለት እነዚህኑ ሀኔታውን በቅርበት የሚከታተሉ ወገኖችን ላቀረብንላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፣ "ዛሬ የሙስሊሙን ህልውና ከጥፋት ለማዳን ካልቻልን፣ ነገ የሁላችንም ህልውና ዋስትና አይኖረውም። ወያኔ በዚህ ያቆማል ተብሎ አይታሰብም። ነገም ሌላውን ሀይማኖትህን ለውጥ ማለቱ አይቀርም፡፡ **በመሆኑም ሁሉም እትዮጵያዊ ከሙስሊም ወገኑ ጎን በመቆም አብሮ መታገል፣ መሞት መቻል አለበት!!**" በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡







# ኢትዮጵያ

በኢሕአፓ የዲሲ ሪጅን ደጋፊ ኮሚቴ

የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ



አድራሻ 5309 Georgia Ave. NW. 2nd fl. Washington DC 20011

ስ/ቁ 202 291 4217 ኢሜል dc.region.eprp@gmail.com


# ርዕሰ አንቀጽ

## ትግል ላይ ያላችሁ ፤ እስኪ እንያችሁ

ከሰሞኑ ብዙ ጉዳጉድ እየተሰማ ሰነበተ ። የዘረኛዉን አምባገነን ግብአተ መሬት ተከትሎ ወያኔ ንቁሪያ ገመናዉን ሸፍኖ ፤በታሪክ ድንክዬነቱ የምናዉቀዉን መሪዉን "ታላቅ" በሚል ሙከሻ አጅቦ ያልፈጠረበትን ቁመና ሊቀጥልለት የጀመረዉን መዋተት ቀጥሎበታል ። ኢትዮጵያዊነት በቁም ሲያቃዠዉ ኖሮ ከመቃብሩ የወረደዉ ለገሰ ዜናዊ ባለራዕይ ተብሎ ሲወደስም ተደምጧል። አዲሱ ስዩመ ወያኔ ኃይለማሪያምም ኒዉዮርክ ድረስ መጥቶ በተመድ ስብሰባ ላይ ሳይቀር የሙት ወያኔ ቅርስ ባለአደራነቱን በይፋ አሳዉቆ ተመልሷል። ይህ ሁሉ ፤ ለወያኔ ጉደኛነትና ይሉኝታ ቢስነት ማለቂያ እንደሌለዉ ጠንቅቀዉ የሚያዉቁቱን ወገኖች እምብዛም አያስደምምም። የወያኔ ካድሬዎች በተገኘዉ አጋጣሚ ሁሉ የዘረኛዉን አምባገነናዊ ሥርዓት ዘላለማዊነት መለፈፋቸዉ የሚጠበቅ ነዉ። ይህ አገልግሎታቸዉ ሥርዓቱ መሬት ከድቶት እስኪገረሰስና ከተቀመጡበት የሥልጣን ሰገነት ላይ ተገፍትረዉ እስከሚወድቁባት ዕለት ድረስ ይዘልቃል።

የሚያስደንቀዉ ጉዳይ በተቃዋሚዉ ረድፍ ሰልፍ ካበጁትና ለሕዝብ ሙብት ልዕልና ትግል ላይ መሆናቸዉን በአንክሮ ከሚነግሩን ወገኖች መሃከል ጥቂቶቹ ነፋስ በሌለበት ሲያስነሱት የከረሙት አቧራ ነዉ ። የዘረኛዉን ሥርዓት ቁንጮ ሞት በማስታከክ ራሱን በሽግግር መንግሥትነት ከሰየመዉ ስብስብ ከተሰማዉ " የእወቁን ደግፉን " ተማጽኖ አንስቶ የተለያየ ቅኝት ያላቸዉ ጫጫታዎች ተደምጠዋል። ከፊሎቹ ለተተኪዉ ጠቅላይ ሚ/ር ተብዬ "ፋታ" እንዲሰጠዉ ይሞግታሉ። ከፊሎቹ ደግሞ ሥዩመ ወያኔዉ ኃ/ማሪያም በፈጣሪ አለቃዉ ወንበር መቀመጡን በራሱ የትግላቸዉ ግብ መዳረሻ አድርገዉታል። ኢትዮጵያ ዉስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር መደረጉን ያለ አንዳች ሀፍረት የነገሩንም አሉ። በግል ደብዳቤ የጻፉለትም መኖራቸዉን ጸሀፊዎቹ ራሳቸዉ ነግረዉናል። በዚህ መሰሉ ፖለቲካ አይሉት ጨረባ መሃከል ፤ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ለወራሴ መንግሥትነት ከመታጨቱ አስቀድሞ፤ ሐዋሳ ሎቄ ላይ ባሳረዳቸዉ ዜጎች ደም እጁን በማጨቅዬት ለአገዛዙ ያለዉን ታማኝነት ያስመሰከረ ሰዉ መሆኑ ተዘንግቷል ። የነርሱ "ቴክኖክራት" ለደቡብ ኢትዮጵያዉያኑ ሲዳማዎች ሰዉ በላ ጭራቅ መሆኑ ግና በደብዳቤም ሆነ በዲስኩር፤ ከቶ አይሸሽጉት እዉነት ነዉ ።
ርግጥ ነዉ በጸረ ወያኔዉ የትግል ጎራ ብዥታ ሲፈጠር ይህ የመጀመሪያዉ አይደለም። የወያኔንና የሥርዓቱን ተፈጥሯዊ ባህሪና የጸረ ወያኔዉን ትግል ግብ በቅጡ ካለመገንዘብ ጋር የተቆራኙ ብዥታዎች በተደጋጋሚ ጊዜያት አጋጥመዋል። አንድም፤ ወያኔ ሥራዉ አድርጎ የሚቀይጣቸዉ ሰርጎ ገቦች፤ አንድም ደግሞ ያላቸዉን ዝና በመጠቀም ትግሉን የማይደርቅ የጥቅም ምንጭ ለማድረግ ያቀዱ ግለሰቦች በየፊናቸዉና በጋራ የሚያደርጉት ጥረት ከየዋሃኑ ዜጎች ዝንጋዔ ጋር እየተዳመረ ሕዝባዊዉን ትግል ከትርምስ አዙሪት ዉስጥ እንዳይወጣ አድርጎታል ። በሰበቡም ሕዝባዊዉ ትግል ደጋግሞ ተመትቷል። በተመሳሳይ ብልጦች መላልሰን ተሞኝተናል። ይህም በተራዉ ለአዲስ ዴሞክራስያዊ ዘመን ጥባት ድልን ተስፋ ባደረጉ ኢትዮጵያዉያን ስሜት ላይ ያሳደረዉ ተጽዕኖ የአሉታ ነዉ። ካለፈዉ ስህተት ለመጪዉ ጊዜ የሚጠቅመንን ትምህርት ለመቅሰም አልታደልንም። ያሳዝናል ። ትግሉ ያለቅጥ ተራዘመ ብለዉ ለክስ የሚነሱ ሁሉ፤ ከሁሉ አስቀድሞ ምክንያቱን ከዚሁ ዉስጥ መፈለግ የግድ ይሆንባቸዋል።

ሲመች ሲመች ፤ከትግሉ ጎራ ቆሞ ጥቂት መፈክሮችን በማጮህ ፤ ሳይመች ደግሞ ከወያኔዉ ካምፕ ያለፈቃዳቸዉ የተቀነሱ የቀድሞ ወንጀለኞችን በአጃቢነት በማገልገል፤ ከሁለት ትዉልድ በላይ የዘለቀዉን ትግል ከዳር ማድረስ አይቻልም። የብዙሃኑ ወገን እየሞተና እየደማ ፤ ጥቂቶች እየተሙለጨለጩና ትግሉን በተገኘዉ ዋጋ ለጠላት እያስረከቡ መቀጠል አይቻላቸዉም። ከወያኔም ሆነ ከአዲሱ ጠ/ሚኒስትር ተብዬ የሥልጣን መንበር ሥር በመንበርከክ የሚደረግ ተማጽኖ ራስን ከማስገመት ወዲያ ርባና እንደሌለዉ በዚህ መሰሉ ርካሽ ዝና አዳኝ ተግባር ላይ የተሰማሩት ወገኖች ጠንቅቀዉ ሊያዉቁት ይገባል። ሕዝቡም ቢሆን በዚህ ረገድ ማስታወቂያ ለለጠፈ ሁሉ አዳራሽ ሞልቶ " ሆ" ባይነቱን ሊያቆም ግዴታዉ ነዉ። ታጋይ ከትግል አንጻር ይመዘናልና ፤ ከጭፍን ድጋፍ አስቀድሞ " ድጋፉ በርግጥ ሕዝባዊዉን ትግል አንድ እጽቅ ያህል ፊቅ የሚያደርግ ጠቀሜታ እንዳለዉ ፈትሾ ማረጋገጥ የግድ ይሆንበታል ።

ዴሞክራስያዊዉ ሕዝባዊ ትግል ያቸንፋል/

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር/

# ደብዳቤዎች

## ስንት ድንጋይ አለ?

መድረክ የተሰኘው አፍቃሪ ወያኔ በዛን ሰሞን እዚህ ዋሽንግተን ዲሲ ወስጥ ስብሰባ ባደረገበት ወቅት፣ ስዬ አብረሃን እና ገብሩ አስራትን፣ የቀድሞ የወያኔ ፈላጭ ቆራጮችን አጅበው የመጡት መራራ ጉዲናና ተመስገን ደሳለኛ ነበሩ፡፡እነዚህ ሁለት ግለሰቦች በ 97 ምርጫ ወቅት ህዝቡ ፓርላማ እንዳትገቡ እያላቸው ወደ ፓርላማ የገቡ እና ለወያኔ እውቅና በመስጠት የመራጩን ህዝብ ቅስም የሰበሩ ሲሆን፣ አሁን ደግሞ ወያኔ ከፓርላማ ሲያባርራቸው የቀድሞ ወያኔዎችን ሥልጣን ላይ ለማውጣት አጃቢ በመሆን እያገለገሉ ናቸው፡፡ስትሄድ እንቅፋት የመታህ ድንጋይ ስትመለስ ከደገመህ ድንጋዩ አንተ ነህ የሚለው ሶቅራጥስ ነው? አይ ሶቅራጥስ አሁን ዘመን ላይ ቢመጣ ስንት ድንጋይ እንዳለ ይታዘብ ነበር፡፡

ደሳለኝ--ከዲሲ

## የወያኔ ታማኝ ወይስ...

በወያኔ የተመደበው እና ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆኖ እንደመጋዣ እንዲያገለግል የተመረጠው ሀይለ ማሪያም ደሳለኝ በተመረጠ ማግስት፣ አንዳንድ ወገኖች፣ ፈሪያ እግዚአብሔር አለው፤ ቢያንስ የማይሳደብ ጨዋ ግለሰብ ነው፤ ትንሽ ገዜ እንስጠው ማለታቸውን ታዝበናል፡፡ እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነው፡ ይህን የመሰለ አስተያየት ለመስጠት የበቁት በፖለቲካ ድንቁርና ነው ወይስ በታማኝ ተቃዋሚነት?

አትንኩኝ--ከቨርጂኒያ

**ውድ 21** ለወያኔ አፍቃሪዎች ይደርስ ዘንድ የላኩት መልክት ደርሶናል። በቦታ ጥበት ምክንያት ባለማውጣታችን ይቅርታ እንጠይቃለን።

የኢትዮጵያ ጋዜጣ አዘጋጆች

**ጤና ይስጥልኝ** ለኢትዮጵያ ጋዜጣ አዘጋጆች በሙሉ እንደምን ከረማችሁ። የመጀመሪያውን እና ሁለተኛውን ዕትማችሁን አንብቤዋለሁ። በይዘቱም ሆነ በአቀራረቡ በጣም ተመችቶኛል። እንዲሁም ደግሞ እንደ እኔ ላሉ በብዛት ዜና ለማይደርሳቸው ወገኖች እንደምታደርሱ ባለሙሉ ተስፋ ነኝ ። እንዲሁም ደግሞ በሃገር ውስጥ ለሚገኙት ወገኖቻችን እንደ ቀድሞዋ ዲሞክራሲያ ወይንም ደግሞ እንደ ዲሞ በህቡም ቢሆን በሃገር ውስጥ እንደምታደርሱ እተማመናለሁ። ስለዚህ እሰይ እሰይ ዕደጉ ተመንደጉ እያልኩኝ ይህችን ግጥም ምን አልባት ለጋዜጣችሁ የምትሆን ከሆነ ብታወጡልኝ መልካም ነው በማለት ልኬላችሁ አለሁ፡ በሚቀጥለው እስከምንገናኝ በቸር ቆዩኝ በማለት የምሰናበታችሁ የናንተው ሸንተም ሹቢሳ ነኝ ።

ዳቢሎስ በልቡ

ዴያቢሎስ የሚሉት የመጥፎ ምሳሌ
ሰውን የሚመስለው ቢታጠቅ ቦላሌ
እሱም ከልብ ገብቶ ካደረ ከሰው
በሚሰራው ሥራ በጨካኝነቱ የሚታወቀው
እኔንም ትዝ ሲለኝ ድሮ የነገሩኝ መምሬ መነኩሴው
ሰይጣኑን አየሁት ገብቶ ከሃገሬ
የሻአቢያ ውላጅ የደደቢት አውሬ።

ውድ ሸንተም ሹቢሳ ይህንን ግጥም ስለላኩልን ከልብ እያመሰገንን በቦታ እጥረት ምክንያት ግጥምዎን ሙሉ ለሙሉ ባለማውጣታችን ይቅርታ እንጠይቃለን።

የ ኢትዮጵያ ጋዜጣ አዘጋጆች

# ዜና ዘገባ

## ቋንቋ ካልቻላችሁ ዜግነት አታገኙም ተባለ

ከ 11/2012 (እኤአ) ጀምሮ የካናዳ ዜጋ ለመሆን የፈለገ ማንኛውም ስደተኛ ቋነቋውን እንደካናዳውያን መናገር መቻል አለበት መባሉን ዊንፒግ ፈሪ ፕረስ የተሰኘው ሚዲያ በድህረ ገጹ ዘገበ፡፡ በዚሁ መሰረት የካናዳ ዜግነት ለማግኘት የሚያመለክቱ ስደተኞች በካናዳ የሚነገሩትን ፈረንሳይኛ ወይም እንግሊዘኛ መቻላቸውን የሚያመለክት መረጃ ማቅረበ ያለባቸው ሲሆን ይህ ሁኔታ በካናዳ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው ተብሏል፡፡ በካናዳ የስደተኞች ሸንጎ፣ ዜጋ መሆን በጣም አስቸጋሪ፣ በገንዘብም በኩል እጅግ ከባድ እየሆነ ነው ይላል፡፡
እንደመንግስት ግምት ከሆነ፣ሃያ ሰባት ከመቶ የሚሆኑት አመልካቾች የቋንቋ ችሎታቸውን የሚያረጋግጥ ዶክመንት ስለሌላቸው ፈተና ለመውሰድ መክፈል እንዳለባቸው ታውቋል፡፡ጃኔት ዴንች የተባሉ የሸንጎው ዳይሬክተር እንደሚገምቱት ከሆነ፣እያንዳንዱ ስደተኛ ለፈተናው $250 የካናዳ ዶላር መክፈል ይኖርበታል፡፡ ወደ ካናዳ የሚመጡ ስደተኞች እንግሊዘኛ ወይም ፈረንሳይኛ ቢናገሩም፣ሁለተኛ ደረጃ የጨረሱበት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የላቸውም ይላል ሸንጎው፡፡ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ አንደኛው፣ሰደተኞቹ ካገራቸው ተገደው የወጡ በመሆናቸው ሲሆን፣ሌላው ደግሞ ቋነቋውን ኢ-መደበኛ በሆነ መንገድ የተማሩ በመሆናቸው ነው ብሏል፡፡ የካናዳ የፌደራሉ መንግስት ቃል አቀባዮች፣ የቀንቋውን ጥናት ተከትሎ የሚገኘው ገቢ ላገሪቱ መልካም አጋጣሚ ነው ይላሉ፡፡ በዊንፒግ ካናዳ የሚገኘው የኢትዮጵያውያን ሰደተኞች ድመጽ በመሆን የሚታወቀው እና ዜግነታቸውን በቃል ፈተና ላገኙ ስደተኞች አስተርጓሚ በመሆን የሚያገለግለው አሊ ሰኢድ ግን ሁኔታውን "ሚዛናዊ አይደለም" በማለት፣ዜግነት የማግኘቱ ጉዳይ አናሳ ለሆኑት ስደተኞች የማይደረሰበት እየሆነ ነው ይላል፡፡ሰደተኞቹ ካናዳ የገቡት በህገ ወጥ መንገድ ሳይሆን፣ከሀገራቸው በሀይል ተገፍተው መሆኑ፤ በተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽን ስደተኘነታቸው የተረጋገጠና በካናዳ መንግስት ተቀባይነት ያገኘ፤ እንዲሁም ስደተኞቹ የካናዳን ህግ የሚያከብሩና ቀረጥ የሚከፍሉ ናቸው ካለ በኋላ፣ "እመኑኝ ስደተኛ መሆንን የሚመርጥ ማንም ሰው የለም" ሲል ለዊንፒግ ፍሪ ፕረስ ተናግሯል፡፡ አሊ ሰኢድ፣ከዛሬ 30 ዓመት በፊት የፖለቲካ ስደተኛ ሆኖ ዊንፒግ ከመምጣቱ በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ እጅግ የከፋ ግርፋት የደረሰበት ሰው መሆኑን የገለጸ ሲሆን፣እሱ የዜግነት ፈተናውን በወሰደበት በ1987 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ፈተናው በጣም ቀላል ነበር፤ አሁን ግን ከባድ ሆኗል ይላል፡፡ እንደ አሊ አባባል ከሆነ፣ስደተኞቹ ከቤታቸው ተወስነው የሚቀመጡና እዚህ ከተወለዱት ጋር ቢገናኙም በጣም ከጥቂቶች ጋር በመሆኑ ቋንቋውን ለመማር እድሉ አይኖራቸውም፡፡
ለምሳሌ ይላል አሊ፤ቺሎት ዘገየ የተባለችው ሴት ሦስት ልጆች አሏት፤እንደ ብዙዎቹ ስደተኞች ከቤት ተወስና የምትቀመጥ እናት ናት፤ባሏን እና ልጆቿን ትንከባከባለች፤ከእንግሊዘኛ ተናጋሪዎች ጋር እትምህርት ቤት ወይም እሥራ ቦታ ስለማትቀላቀል ቋንቋውን ለመማር አጋጣሚውን አላገኘችም፡፡ስለዚህ ዜግነት የማግኘቱ ነገር ለሷ ከባድ ይሆንባታል ይላል፡፡

## ኢትዮጵያወቷ ከባርነት ተላቀቀች

በዱባያ የቤት ሠራተኛ ሆና ስታገለግል የነበረች አንዲት ኢትዮጵያዊት ወጣት ከቀጣሪዎቿ የባርነት ቀንበር ተላቃ ነጻ መውጣቷን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ኢትየጵያዊቷ ነጻ ልትወጣ የቻለችው፣ዱባይ የሚገኙ ቀጣሪዎቿ ፈረነሳይ ፓሪስ በመጡበት ወቅት ነበር፡፡ ይህቺን ወጣት ነጻ ልታወጣት የቻለችው፣ የልጅቷ ቀጣሪ የነበሩት ግለሰቦች ባረፉበት ሆቴል ውስጥ ትሰራ የነበረችውና የዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት አመራር አባል የሆነች የሆቴሉ ሰራተኛ መሆኗንም ለማወቅ ተችላል፡፡በዱባይ በባርነት ቀንበር ሥር ስትሰቃይ የነበረችው ወጣት ቀጣሪዎቿ ፓሪስ በሚገኘውና ፓሪዘ ሳን ላዛር ኮንኮርድ በተሰኘው ሆቴል ውስጥ ለማረፍ ሲገቡ፣ በሆቴሉ ውስጥ ትሰራ ለነበረችው ኢትዮጵያዊት ወገኗ በምን ሁኔታ ውስጥ እንዳለች ትነግራታለች፡፡ኢትዮጵያዊቷ ወጣት በዱባይ ለሚኖሩስምንት አባላት ላለው ቤተሰብ ሥትሰራ፣ ስብእናዋን ከሚያዋርድ ስድብ አንስቶ እስከ ድብደባ የሚደርስ ስቃይ ይደርስባት እንደነበርና ከአመት በላይ ደሞዝ እንዳልተከፈላት በሆቴሉ ውስጥ ላገኘቻት ኢትዮጵያዊት ወገኗ ገለጸችላት። ይህን በደል የተረዳችው ወገንም በፓሪስ ለሚገኙ ጸረ-ዘመናዊ ባርነት ተቋሞች ሁኔታውን አሳወቀች። እንዚህ ተቋማትም እንቅስቃሴ በማድረግ ከላይ የተጠቀሰችውን ወጣት ከዘመናዊ ባርነት ነጻ እንድትወጣና እዛው ፓሪስ ከተማ ውስጥ በመቅረት የነጻነት አየር እንድትተነፍስ አስችለዋል፡፡ ይህን ተከትሎ የሆቴሉ አስተዳደር የኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ሴቶች ድርጅት የፓሪስ ቅርንጫፍ አመራር አባል ለሆነችው ኢትዮጵያዊት፣ ማስጠንቀቂያ እና ማስፈራሪያ በመስጠታቸው፣ የሆቴሉ ሠራተኞች ማህበር እባላት የሆቴሉ አስተዳደር የወሰደውን እርምጃ በመቃወም በሆቴሉ ደጃፍ በ 10/3/ 2012 ( እ.ኤ.አ) ደማቅ የተቃውሞ ሰልፍ አድርገዋል፡፡

## ሁለት ኢትዮጵያዊያን ህጻናት ከፍተኛ ስቃይ ደረሰባቸው

እዚህ አሜሪካ ፔንሲልቫኒያ ውስጥ የሚገኘ አንድ ምክትል ጠቅላይ አቃቤ ሕግ እና ሚስቱ ከኢትዮጵያ በጉዲፈቻ ያመጧቸው ህጻናት ላይ ከፍተኛ የአካል ጉዳት እንዳደረሱባቸው አሶሼትድ ፕረስ ዘገበ፡፡ እንደ ዘገባው ከሆነ፣ልጆቹ ለህክምና ወደ ሆስፒታል በሄዱበት ወቅት፣ የ6 ዓመቱ ወንድ ልጅ በምግብ እጦት መጎዳቱን እና የሰውነቱ ቆዳ ደግሞ አባብጦ መገኘቱን፤ እንዲሁም የ18 ወሯ ሴት ልጅ ደግሞ የራስ ቅሏ ላይ በርካታ ቦታ የአጥንት ስብራት ምልክት እንደሚታይባት የሆስፒታሉ ዶክተር በምርመራ ወቅት ማረጋገጡን የካውንቲው ፖሊስ ተናግሯል፡፡ልጆቹ ከእውነተኛ ቤተሰቦቻቸው ጋር ምንም አይነት ግኑኝነት እንደሌላቸለውና ከዚህ በኋላ ሴቷ ልጅ ከጉዲፈቻ አሳዳጊዎቿ ጋር ከኖረች እደገና ጉዳት ሊደርስባት ወይም ልትሞትም እንደምትችል ተነግሯል፡፡

**ድርጅትዎን በፍኖተሕብረት ሬዲዮ ያስተዋውቁ**
**አድራሻ 5309 Georgia Ave. NW**
**Washington DC 20011**
**ስ/ቁጥር 202 291 4217**
**e-mail:**
**dc.region.eprp@gmail.com**

# ምን ይሰማ... አገር ?



### - "ሻቢያ ምን እያሰበ ነዉ ?'

ተስፋዬ ገብረአብ ፤በኢትዮ ሚድያ ፎረም ድህረ ገጽ ፤አክቶበር ፲፬ ቀን ፪፻፻፲፪ ያሰፈረዉ፤
* ወይ ጉድ / "የሻቢያ መንገድ" ብለዉ ከሚጽፋልን ዉስጥ አወቆች ሃሳቡ ተሰዉሮ ነዉ ጥያቄዉ ? የላይኛዉ ቤት አምባገነን ተራዉን እስኪገነደስ ጠብቅና መልሱን ጭምር ትጽፍልናለህ ፡፡

### - "ኢኮኖሚያችን ከ፲፩ በመቶ በላይ እያደገ ነበር ፤......"

ሬዉተርስ የጠቅላይ ሚኒስትር ተብዬዉን የፓርላማ ወሬ ጠቅሶ አክቶበር ፲፯ የዘገበዉ፤
• "ከለማበት የተጋባበት" መባሉ አግባብ አለዉ ፡፡ ሳይበረዙ ሳይከለሱ የሚንከባከቧቸዉ የሰዉዬዉ ራዕዮች የ'፲፩ ቁጥር አባዜያቸዉንም ያካትታሉ እንዴ?

### - "አዜብ መስፍን ቤተ መንግሥቱን ለቅቃ ለመዉጣት አሻፈረኝ አለች ፤"

ዴይሊ ኔሽን ፤ አክቶበር ፲፬ ቀን ፪፻፻፲፪
* ኧረ የሴትዮዋን ስም አታጥፉ ፤ቀድሞ ነገር ማን ደፍሮ ጠየቃትና?

### - "ኃ/ማርያም ደሳለኝና ኤርትራዊው ሚስቱ"

ኢትዮሚድያ ድህረ ገጽ ፤አክቶበር ፲፱ ቀን ፪፻፻፲፪ እንዳሰፈረዉ፤
በተሰቀለዉ / ለማስረጃ የሚሆን የልደት የምስክር ይዛችኋል? በስም ከሆነማ ስንትና ስንት መለስ የሚባል ጉራጌ አለላችሁ ፡፡ ደግሞ ቢሆንስ ፤ ይቅርና ወላይታ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ዉስጥ የተወለደ ሕጻን ኢትዮጵያዊ ነዉ -በዘሩ ጥልያን እንኳ ቢሆን ፡፡

### - "በሀገራችን እጅግ እየበዛ የመጣዉን የዕብድ፤የለማኝና የሰካራም ቁጥር አንድዬ ልጓም ያብጅልን"

ይነጋል በላቸዉ ፤ "ካለበት የተጋባበት" ፡ ኢትዮላይን ድረ-ገጽ ላይ ካስነበቡት፤
• ይኼ ከ፳ቱ ዓመታት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ስኬታማነት ጋር የሚቃረን የኪራይ ሰብሳቢነት፡ የትምክህተኛነት፤ ወዘተ ....አስተሳሰብ ነዉ ፡፡ ...ለነዚህ ሁሉ የዕድገት መመዘኛዎች ልጓም ከተበጀላቸዉ ...እንደምን አድጋችኋል ልንሰኝ ነዉ ?

በየጊዜው አመቺና ለውጥ ልናመጣባቸው የምንችልባቸው ጊዜዎች እየተከሰቱ ሲያመልጡን ተቃዋሚ ሀይሎችን ማውገዙ የተለመደ ነው:: አልተባበሩም ነው ቀዳሚው ወቀሳና ቁጭት:: ሀቅ ነው ተቃዋሚ ሀይሎች ጥርስ ያለው ወያኔን የሚነክስ፣ የሚቦጭቅ ትብብር ማድረግ ካቃታቸው ዓመታት ተቆጥረዋል:: ይህ ለምን ሆነ ለሚለው ጥያቄ መልሱ ራሱን የቻለ ርዕስ ነው:: ግን ለመሆኑ ህብረት ስንል ምን ማለት ነው? ከዚያ በፊትስ ድርጅት ስንል ለመሆኑ ምን ማለታችን ነው:: ገበና ማስጣትና ወሳኝ ሀቅን ከእርምት አንጻር ማቅረብ የተለያዩ ናቸው:: ያሰብከው ዓላማ አልሆን ብሎ ሲከሸፍ ሁኔታው ሲጠጥር ጠጣሩ እንዲላላ የላላውን ወጥር ብሎ ታዋቂው ገጣሚ ሀይሉ ገብረ ዮሐንስ (ገሞራው) እንደመከረው ሁሉ የህዝብን ጎራ ድክመት አውቆ ለማረም መነሳት ወሳኝ ነው፡ የላላው ካልተወጠረ ትግል ወደ ድል አያመራምና:: ስለዚህም በድክመት ላይ ብናተኩር ተጠናክረን ወደፊት መጓዝ እንችል ዘንድ ነው:: የወዳጅ ሂስ አይጎዳም፣ አያምም::

በየወቅቱ የሚከሰቱ አመቺ ክስተቶችን ተጠቅመንባቸው ለህዝባዊ ድል ልንደርስ አለመቻላችን በየተጨባጩ ሁኔታና ወቅት የየራሱ ምክንያት አለው:: ለምሳሌ በየካቲት 66 ብቅ ያሉት እነ ኢሕአፓ በቂ አቅምና ጉልበት አልነበራቸውም ለስልጣን ለሙብቃት:: ከዚያም በኋላ በርከት ያሉ ዕድሎች ተነውብናል:: ለምን? ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ተቃዋሚ ሀይሎች ተባብረው ባለጉልበት አለመሆናቸውን ይመለከታል:: በ1997 ተቃዋሚ ሀይሎች በተለየም ህብረትና ቅንጅት ባይተባበሩም አንዳንድ የህብረት መሪዎች ተጎንባሽነትና የቅንጅት አንዳንድ መሪዎች በአፍቅሮ ወያኔና ባዕዳን መቀሰፍ ድልን ቢያርቅም፣ ሁኔታው የወያኔን ሽንፈት ማብሰሩ የሚካድ አይደለም:: ሕልው የሆነና ምንነቱን ማንነቱን በሀገር ቤት ያስረገጠ ህብረት ውጤታማ እንደሚሆን ታይቷል ማለት እንችላለን::

ህብረትና ትብብር ለድል አስፈላጊ መሆናቸውን መካድ አይቻልም:: ግን የነማን ህብረት? ምን ዓይነት ህብረት? ብሎ መጠየቅ ደግሞ የግድ ነው:: ድርጅትንና መደራጀትን ለጊዜው ትተን ህብረትና ማበር ላይ ስናተኩር ለትንተና መሰረት የሚሆነን ሰፊ የሆነ የህብረት መሰረተ ተመክሮ ቅርስ አለን:: ረጅም ጉዞ ተጉዘንበታል::

በኢሕአፓ ተመክሮ እንኳን አየሌ የህብረት ጥሪትና ስብስቦችም ነበሩ:: እንዱ ሲደናቀፍ ሌላን እየሞከረ ድርጅቱ የጋራ ክንድን ለማጠናከር ያደረጋቸው ሙከራዎች በታሪክ የተመዘገቡና አልፎም ትምህርታዊ ናቸው:: የቅርቦቹን ብናይ እንኳን ከኢዴሀቅ እስከ ህብረት የተደረገው ሙከራ በቀላሉ የማይታይና አይረባም የሚባል አይደለም:: ውጤትም ነበረው። ትግሉንም አስቀጥሏል:: ሰፊውን የህብረት ጥረት ሻጥረኞች አደናቅፈው

# ድርጅት ስንል መደራጀት፤ህብረት ስንል መተባበር

በጎን የራሳቸውን ቅንጅት በቶሎ ቢያቋቁምም ይህ ስብስብ ከመኢአድ ውጭ ነፍስ ያላቸውን ቡድኖችን የሰበሰበ ባለመሆኑ፤ በመሰመርም ሆነ በአቋም ደረጃ የማይስማሙ ቡድኖችን ያቀፈ በመሆኑ ገና ከጅምሩ ዘላቂነቱ አጠራጣሪ ነው በማለታችንም ብዙዎች ውግዘትን ወርውረው ነበር:: የድርጅት ይዘትና ምንነትን በተመለከተም በዚሁ ጥያቄ የተነሳ ነበር፤ቀጥለንም የምናየው ይሆናል:: ጫጫታና አጉል ተስፋ ሌላ፤ ሀቅ ሌላ ሆና ግን ያው ክፍፍሉና ውድቀቱ ተከሰተ:: ህብረትም ቢሆን መከፋፈልንና መዳከም አልቀረለትም:: ለምን ስንል የሚከተሉትን ዋና ሀቆች መገንዘብ እንገደዳለን::

**1.**የሚሰበሰቡት ማን ጠላት ማን ወዳጅ በሚለው ላይ እንኳን ተመሳሳይ ግንዛቤ የላቸውም::

**2.**የሚሰባሰቡት አንዳንዶቹ ድርጅታዊ ህልውና ሲኖራቸው ሌሎቹ ደግሞ የሁለት ሦስት ሰው ''ስብስቦች'' ናቸው:: ይህ በህብረቱም በቅንጅትም ለምሳሌ የተከሰተ ነው:: በመሆኑም በሀገር ቤቱ ትግል ላይ ምንም ጫናና ሚዛን የነበራቸው አልነበሩም ብዙዎቹ::

**3.**ዛሬ በህብረቱ ስም ተሰባሰብን የሚሉት ቢደመሩ ከ 20 የሚበልጡ አባላት የሌላቸውና በሀገር ቤት ደግሞ ሁለትም አባል ያጡ ናቸው::

**4.**የነመድረክ ዓይነቶቹ ደግሞ የኢሠፓና ወያኔ ስብስብ ከመሆናቸው ሌላ ቀደም ሲል ጥላቸው ከወያኔ ሳይሆን ከመለስ ነው ሲባል የቆየ ቢሆንም ዛሬ ደግሞ ከመለስም ጠብ እንደሌላቸው ማወቅ ተችሏል::

**ለዚህም ነው ህብረት ስንል ህያው ከሆኑ፤ህልውና ካላቸውና በሀገር ቤት ትግሉም ሚዛንና ክብደት ካላቸው፣ ለባዕድ አሽከር ካልሆኑት ድርጅቶች ጋር ይሁን የምንለው::**

ሦስት አራት ሆነው በባዕድ ሀገር ድርጅት ነን ከሚሉት ጋር መተባበር ፋይዳ ቢስ መሆኑን በዓመታት ተመክሮ አይተነዋል:: ህብረት ስንል ቧልት አይደለም:: የሚታገሉና ነፍስ ያላቸው ፀረ ወያኔ ድርጅቶች ህብረት ማለት ነው:: ህብረት ስንል ተሰባስቦ ከወያኔ ሸቦጥ ወይም ጫማ ስር ለመውደቅና ታሪክን ብሎ ለመለመን ሊሆንም አይችልም:: ህብረት ገና ከመነሻው ፀረ ወያኔ መሆን አለበት::ህብረት ከመነሻው ለባዕድ ያደረና ለባዕድ ትዕዛዝ ተገዢ ሊሆን አይችልም::ነፃና ህያው ድርጅቶች በትግሉ መድረክ ማለትም በሀገር ቤት ተግባራዊ ትብብር ሊያደርጉ ከተነሱ መደገፍ አለባቸው::

በጉንጭ አልፋ ጫጫታ በባዕድ ሀገር ህብረት፤ ጥምረት ውህደት ወዘተ እየታበለ የሚካሄደው ሁሉ ወያኔን ሊያስፈራው ቀርቶ የሚያስቀውና ድንቁም ተቃዋሚ ድንቁም ህብረት ብሎ ሊያሾፍብን ዕድል የሚሰጠው ነው::

እዚህ ላይ መነሳት ያለበት አቢይ ጉዳይ ድርጅትን ይመለከታል:: አመቺ ሁኔታዎችንም መጠቀምና ዘላቂ ለውጥ ማምጣት ያልቻልነው በህብረት አንጻር መድከማችን ብቻ ሳይሆን ድርጅት መሆን መደራጀትና ማደራጀትም ስላቃተን መሆኑ መነገር ያለበት ነው:: ድርጅት ስንል ድርጅት ሲሉ በሚል በተደጋጋሚ ትችት ማቅረብ የግድ የሆነውም በዚህ የተነሳ ነው ማለት ይቻላል:: ድርጅት ስንል ማንነቱን ገላጭ መሰረታዊ ነጥቦች አሉ:: ድርጅት ግልጽ የሆነና ሁሉም አባላቱ የሚቀበሉት መርህ ግብር ወይም ፕሮግራም ያስፈልገዋል:: አመራሩ የሚያቀርበውንና የሚገፋውን አቅዋም አባላት ተጻረው ሌላ የሚያቀርቡ ከሆነ ድርጅት የለም ማለት ተገቢ ነው::

የድርጅቱን መርሀ-ግብር ተብዬውን አመራሩ ከቶም የማይቀበለው ከሆነ በቀን ተቀን ተግባሩና አቅዋሙ ድርጅት አለ ማለት አይቻልም:: ድርጅት አለ ሊባል መዋቅር መኖር አለበት፤ የጋራ አሠራር መኖር አለበት፤ ዲሲፕሊን እና ስነስርአት መኖር አለበት፤ በጋራ በአንድ አቅጣጫና ለአንድ ግብ መንቀሳቀስ መታየት አለበት። ማለትም የሀሳብ አንድነት ፤የድርጅትን ምስጢር መጠበቅ አለበት::በሆነ ሰብሰባ ላይ ተገኝቶ ሆ ያለ ሁሉ የድርጅት አባል ተብሎ ሊወሰድ አይችልም:: ማንኛውም ድርጅት ቢሆን አባል ማን ነው ለሚለው መሠረታዊና ቀዳሚ ጥያቄ መልስ መስጠት አለበት::

አፋኝ ፀረ ሕዝብ የሆነን አገዛዝ ሊታገል የሚነሳ ድርጅት ደግሞ የግድ ድርጅትነትን ለመጠበቅ ሊከተላቸው የሚገባ አሠራሮችና ፖሊሲዎች መመሪያዎች መኖር አለባቸው:: ስለዚህም ነው፤

**1.**የሁለት ሦስት ወይም ሰድስት ሰዎችን ሰብስቦ ድርጅት ብሎ መቁጠርና መውሰድ የማይገባው፤

**2.**በአንፃራዊ ደረጃም በርከት ያለን ሰው ሰብስበው (ማለትም ዛሬ እንደምናየው ሰላሳ አርባ ሆነው) ድርጅት ነን ቢሉም በሀገር ቤት ምንም መሠረት ከሌላቸውና አሰራራቸውም መሳለቂያ ከሆነ እነዚህን ዓይነቶቹን ድርጅት ማለት ስህተት የሚሆነው፤

**3.**ራሳቸውን ኢትዮጵያዊ ድርጅት እያሉ ግን ትእዛዝ ከባዕድ ተቀባይ ከሆኑና ያለውን ስርዓት ሊጠብቁና ሊታደጉ ለተነሱ ተቃዋሚ ድርጅቶች ከቶም አንሰምርም ዝምም አንልም ልንላቸው የሚገባው::

ጉድጓድን ለመቆፈር ዶማና አካፋ ይዘው ይነሳሉ እንጂ ጎራዴን አይታጠቁም:: ለዚህም ነው ፀረ ሕዝብ አገዛዝን ለመታገል ስንነሳ ቆራጥ ድርጅትን እና የሚሰራ ህብረትንም ይዘን መነሳት ያለብን:: የሚታገሉ እና የሚኮሩ መሪዎችን ይዘን መነሳት ያለብን:: ገና እንዲትም ጥይት ሳትጮህ ለጠላት የሚሰግዱትን፣ ለባዕድ የሚንነበሱትን ምሩን ማለትም አይገባንም:: ራሳቸውን ምሁር ልሂቅ ብለው ከሰየሙ የፍርሀትና የክህደት ቋት ዶክተር ፕሮፌሰር በሉን ባዮች ዜሮዎችና ማፈሪያዎች መሪ ይኖሩብናል:: ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ ባላአዳ አይቀበለውም ተብሏልና ትግላችንንና ሀገራችንን እኛው ካላከበርን ማንም አያከብርልንም:: በታሪክ ሂደት ከሀዲ፤ዘረኛ ወያኔ፤ ባንዳ፤ ዜጋን ሻጭ፤ ቡከን ሆነው የቆሸሹትንም ዛሬ ወደ ጎራችን ልናስገባ ከተነሳን ጸያፍ ጥፋት የእኛው ይሆናል:: በራሳችን ላይ ገመዱን አጥብቀናልና:: ገዳዮቻችንን መሪ ብለናልና:: አስመሳዮችን ጀግና ብለን አዳንቀናልና:: ወገኖቻችንን የፊጁትን ነፍሰ ገዳዮች ታጋይ አርበኛ ብለን ሰማዕትን አሳዝነናልና:: ህዝብ ሀገሩን የማዳን ግዴታ አለበት። ማንም ሌላ ሀይል ሀገሩን አያድንለትም:: ለዚህም ነው ድርጅት ማንነው፤የሚፈይድ ህብረት የትኛው ነው ብሎ ማወቅ መረዳት ያለበት:: አስመሳዮችንና የጠላቶቻችን ቡችሎች ተከትለን መቀመቅ እንዳንገባ፣ እንጦሮጦስ እንዳንወርድ:: ወደዚህ ውድቀት ሊመሩን የሚፈልጉትን ሁሉ ወግድ እንበላቸው:: የነገ ዕጣችንና የሀገራችን ባለቤት ሕዝብ መሆን አለበት:: ይህን ሚና ከሕዝብ ሊቀሙ ላይ ታች የሚሉትን ሀሉ እንቃወም፣ እንታገላቸው::

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

**ድርጅትዎን በኢትዮጵያ ጋዜጣ ያስተዋውቁ ! አድራሻ**
5309 Georgia Ave. Nw , Washington DC 20011
ስ/ቁጥር 202 291 4217
e-mail: dc.region.eprp@gmail.com

"አሸምቆ" በሚል ቅጽል ስም ነበር የሠፈር ጓደኞቹ የሚጠሩት ።በተፈጥሮዉ እልኸኛና አትንኩኝ ባይ ፤ በማኅበራዊ ሕይወቱ ደግሞ ከሰዉ ጋር ተግባቢና ተጫዋች ነበር ።በጓደኞቹ ዘንድ ተከባሪ የሆነዉን ያህል ከጠላቶቹ ሳይቀር በአይምሬ ጀግንነቱ አድናቆትን አትርፏል። አራት የትግል ጓዶቹ የሚገኙበትን ቡድን ለፍልሚያ እየመራ ድርጅታዊ ተልዕኮዉን ለመወጣት ከቤቱ ወጥቶ እስከቀረባት ሕዳር ፯ ቀን ፲፱፻፸ ዓ.ም ማለዳ ድረስ በከፍተኛ ፲፩ ቀበሌ 02 ዉስጥ ነበር ኗሪነቱ ። የዚሁ ከፍተኛ የኢሕአፓ ተጠሪም ነበር ።

ጌታቸዉ ጥሩነህ በ፲፱፻፵፪ ዓ.ም መጋቢት ወር በዕለተ ኪዳነምህረት(፲፮) ፤ ገዳም ሠፈር ነበር የተወለደዉ ።ለቤተሰቡ የመጀመሪያ ልጅ እንደመሆኑ በተለይ ወላጅ እናቱ ወጥቶ እስከሚገባ አያምኑትም ነበር ። በዚሁ ጽኑዕ ፍቅር የተነሳም ነበር ፤ በእናቱ በወይዘሮ ጥሩነሽ ወልደኪሮስ ስም ለመጠራት የበቃዉ ።ከ፩ኛ እስከ ፬ተኛ ክፍል አርበኞች ፤ ከ፭ተኛ እስከ ፰ተኛ ደግሞ በቁስቋም (እቴጌ ጣይቱ ብጡል ) ተምሯል ። ከዚያም ከ፱ እስከ ፲፪ኛ ክፍል ድረስ በቀድሞዉ ተፈሪ መኮንን አጠቃላይ ሁለተኛ ት/ቤት ትህምርቱን ተከታትሏል ። ትጉህ ተማሪ ነበር ። በአንድ ዓመት ሁለት ክፍሎችን ያለፈበት ጊዜ የመኖሩን ያህል ከንጉሡ እጅ ሽልማቶችን ለመቀበል የበቃ ተማሪ ሊሆን በቅቷል ።በአለማያና በባህር ኃይል ኮሌጆችም ትምህርቱን ተከታትሏል ።

አለማያ ኮሌጅ ይማር በነበረበት ጊዜ የሃገሪቱ ተማሪዎች በጉልተኛዉ ሥርዓት ላይ ያደርጉት የነበረዉ አመጽ እጅጉን ተፋፍሞ ነበር ። እናም አንድ ወቅት ላይ ጉደር ይገኝ በነበረዉ የራስ መስፍን ስለሺ እርሻ ዉስጥ በጎተራ በተቀመጠ ጤፍ ላይ እሳት ተለቀቀበት ። በእርሻዉ ላይ የነበረዉ የወይን ተክልም ተጨፈጨፈ ።የድርጊቱ ፈጻሚዎች ተማሪዎች መሆናቸዉ በመጠርጠሩ ጌታቸዉን ጨምሮ ከየሥፍራዉ እየታፈሱ ወደ ሰንዳፋ ተወስደዉ ታሰሩ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም በሥራ እንዲቀጡ ከሰንዳፋ ወደ ጎጃም ጠቅላይ ግዛት ተወሰዱ ። ጌታቸዉ ጠያቂ አልነበረዉም ። እንዲያ የሚወዱት እናቱ ፤ እሱን ፤ ታናናሾቹን አንድ ወንድና አንዲት ሴት ልጃቸዉን ጨምሮ አራት ቤተሰባቸዉን የሚያስተዳድሩት ሳንባ ነቀርሳ ሆስፒታል ዉስጥ በጤና ረዳትነት ተቀጥረዉ በሚያገኟት አነስተኛ ደመወዝ ነበርና ወደ ጎጃም ሄደዉ ሊጠይቁት አልቻሉም ።

ከአንድ ዓመት እስራት በኋላ ተፈትቶ ወደ አዲስ አበባ የተመለሰዉ ጌታቸዉ የአለማያ ትምህርቱን አቋርጦ በባህር ኃይል ኮሌጅ በእጩ መኮንንነት ተቀጥሮ ወደ ምጽዋ አቀና ።እዚያም ሳለ በተደጋጋሚ ጊዜ እየታሰረ ተፈትቷል ። ሆኖም ከአራት ዓመታት ቆይታ በኋል ሥልጠናዉን አጠናቅቆ በ፲፱፻፷፫ ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ተመልሷል ። መኖሪያዉን በከፍተኛ ፲፩ ቀበሌ ፪ ዉስጥ በሚገኘዉ የእናቱ ቤት ያደረገ ሲሆን በኢሕአፓ ዉስጥ ተሰልፎ በሕቡዕ መንቀሳቀሱን ቀጥሎበታል ።በዚሁ እንቅስቃሴዉ ወቅት ትጋቱንና ብቁ አመራር ሰጪነቱን ከማስመስከሩም በላይ ከሌሎቹ ጓዶቹ ጋር በመሆን የድርጅታቸዉን ሥራ በትጋት ሲያቀላጥፉ ቆይተዋል።

# ትላንትና

## ተወርዋሪዉ የኢሕአፓ ታጋይ

## ጌታቸዉ ጥሩነህ

(ምንጭ ጎሕ መጽሔት ፤ጥቅምት ፲፱፻፺ ዓ.ም )

ወቅቱ ደርግና የመኢሶን ሎሌዎቹ ኢሕአፓን በጸረ-አብዮተኛነት ፈርጀዉ የተንቀሳቀሱበት ፤ ደም የጠማቸዉ የሥርዓቱ አጫፋሪዎችም ታጥቀዉ ወጣቱን በየአካባቢዉ መፍጀት የጀመሩበት የትንቅንቅ የሽብር ጊዜ ነበር ።ኢሕአፓም በበኩሉ ሕልዉናዉ አጠያያቂ ደረጃ ላይ በወደቀበት በዚያን መሰሉ ሁኔታ ዉስጥ ራሱን መከላከልና አጸፋዉን ለመመለስ በመገደዱ ከጠላቶቹ ከሚላኩበት የሞት መልዕክተኞች ጋር በየአቅጣጫዉ በመፋለም ላይ ነበር ።በዚህ መሰሉ ቀዉጢ ዉስጥ ነበር እንግዲህ ጌታቸዉ ጥሩነህ ድርጅቱን ኢሕአፓን ለመታደግ በፍልሚያዉ ሜዳ ጠላቶቹን እንደወጡ ማስቀረት የጀመረዉ ።በሚደርሰዉ መረጃ መሠረት፤ የደርግ አሳሽ ቡድኖች በሚንቀሳቀሱባቸዉ አካባቢዎች አብዛኛዉን ጊዜ ብቻዉን በመሄድ ፤ በሌላዉ ጊዜ ደግሞ ከትግል ጓዶቹ ጋር በመሆን የዕኩያኑን ግንባር በአረር እየተረከከ ፈጥኖ በመሰወር ኩቶ አቻ አልነበረዉም።

በነበረዉ ፈጣን የትምህርት አቀባበልና በወታደራዊ ቅልጥፍናዉ በአዛዦቹ ሳይቀር የተሞገሰዉ ወጣቱ ጌታቸዉ በምጽዋዉ የባህር ኃይል ኮሌጅ ቆይታዉ የቀሰመዉ ትምህርት፤ በግልም በጓደኞቹ ዘንድ የነበረዉ ተደማጭነት በፍልሚያዉ መስከ የሚሰጠዉን ተልዕኮ ሁሉ ያለአንዳች ግድፈት ለመወጣት አስችሎታል። ጠላቶቹ እስከፍጻሜዉ ድረስ ማንነቱንም ሆነ መግቢያና መዉጫዉን በፍጹም አያዉቁም ነበር ። በስሙ ብቻ ግን ይሸበሩ ፤ በዝናዉ ብቻም ይበረግጉ ነበር ።ይህ ሁሉ ሆኖ ፤ ጌታቸዉ ከምጽዋ ከተመለሰ በኋላ አንድም ቀን እንኳ ከቤቱ ዉጭ አድሮ እንደማያዉቅ ቤተሰቦቹ መስክረዉለታል። ለየት ያለ ድርጅታዊ ሥራ ካላስመሸዉ በስተቀርም ወደቤቱ የሚገባዉ በጊዜ ነበር ።ዘወትር ጠዋት ከቤቱ ሲወጣ የአካባቢዉ ነዋሪዎች ስለሚያዩት የኢሕአፓ ተሳትፎዉ ለረዢም ጊዜ እንዳይታወቅበት ረድቶታል።ከርሱ ይልቅ ተስፋ ሚካኤል ታዬ የሚባለዉ ታናሽ ወንድሙ በኢሕአፓ አባልነት ተጠቁሞበት በአሁኑ ወረዳ `፫ ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ መቆየቱን ስናጤን ጌታቸዉ ራሱን በሕዝብ መሃከል የሰወረበትን ከጥበብ የተጠጋ ብልሃት እናደንቃለን።

## ሕዳር ፯ ቀን ፲፱፻፸ ዓ.ም

የጌታቸዉ ወላጅ እናት ወ/ሮ ጥሩነሽ ወልደኪሮስ በጤና ረዳትነታቸዉ ከሌሎቹ ባልደረቦቻቸዉ ጋር በመሆን ወደ ኤርትራ እንዲዘምቱ ከተደረገ ሰነበተ ።የጌታቸዉ ታናሽ ወንድም ተስፋ ሚካኤልም በኢሕአፓነት ተጠቁሞ ከታሰረ ቆዬ ። ቤቱ ዉስጥ የቀሩት ጌታቸዉና ትንሽ እህቱ ብቻ ነበሩ።ጌታቸዉና አራት የትግል ጓዶቹ ፤ አጸደወይን ሰቡ ዘገየ ፤ ተካ (በቅጽል ስሙ ዛጋምባ)፤እና ጥላሁን (ሁሉም የሸሮ ሜዳ ልጆች ናቸዉ ) ከ ጌታቸዉ የኋላሸት ጋር በመሆን በዕለቱ የመጨረሻዉን የከተማ ዉስጥ ግዳጃቸዉን ከተወጡ በኋላ አሲምባ ፤ ካልሆነም ሱዳን ለመግባት ወስነዋል ። ደብረብርሃን ተወልዶ ጨርቆስ ያደገዉ ጌታቸዉ የኋላሸት ከስመ ሞክሼነታቸዉ ወዲያ ለጌታቸዉ ጥሩነህ የቅርብ ጓደኛዉ ነበር። ባህር ኃይል ኮሌጅ አብረዉ በዕጩ መኮንንነት ሲሰለጥኑ ከመቆየታቸዉም በላይ አብረዉ ጠፍተዉ ወጥተዋል።እናም ጌታቸዉ ጥሩነህ በዚያን ዕለት ማለዳ ፤ እህቱ ስምረት ደመረ ያቀረበችለትን ቁርስ ከተመገበ በኋላ ጓደኞቹ ዘንድ ደርሶ እንደሚመለስ ነግሯት ከቤት ወጣ።ከአምስቱ የኢሕአፓ ጓዶቹ ጋር ቀደም ብለዉ ከተቀጣጠሩበት ቦታ ከተገናኙ በኋላ በተመደበላቸዉ ኩምቢ ቮልስዋገን መኪና ተሳፈሩ ። የዚያን ዕለቱ ዒላማቸዉ ጭራቁ የደርግ ሰዉ በላ ቀልቤሳ ነገዎ ነበር ። ግንባሩን በአረር ለመፈርከስ ተሰናድተው ፤ ወደሚገኝበት ከፍተኛ ፱ ገሰገሱለት ።

ደርግ ምስጢሩን እንዴት ሊደርስበት እንደቻለ እንቆቅልሹ እስከዛሬም አልተፈታም ። አምስቱን ጓዶች ጭና የምትገሰግሰው ኩምቢ ቮልስ ቀጨኔ ድልድይ ላይ እንደደረሰች አንድ መሳሪያ የታጠቀ ሰዉ በድንገት ከተሸሸገበት ወጣና እንዲቆሙ የግዳጅ ምልክት ሰጣቸዉ ። እንደተባሉትም አደረጉ ። ሰዉዬዉም ወዲያዉኑ ወደመኪናዋ ቀርቦ መታወቂያቸዉን እንዲያሳዩት አዘዛቸዉ ።ጌታቸዉ ጥሩነህ መታወቂያዉን አዉጥቶ በማሳየት ላይ ሳለ መከበባቸዉን የተገነዘቡት ጓዶች አንዳች ፈጣን ርምጃ መዉሰድ እንደሚገባቸዉ አምነዉበታል ። እናም አጸደወይን ከመኪናዉ ወርዳ በስተጀርባዉ ዞረችና ወታደሩን መትታ ጣለችዉ ።በዚያዉ ቅጽበት ደፈጣ ላይ የነበሩት በርካታ ወታደሮች ካደፈጡበት ሆነዉ እንዳይነቃነቁ አዘዟቸዉ ። አምስቱ የኢሕአፓ ጓዶች ግን ትዕዛዙን ከቁምነገር ሳይጽፉ የነፍስወከፍ መሣሪያዎቻቸዉን በፍጥነት አንስተዉ ከመኪናዋ በቅልጥፍና ወርደዉ ከግዙፉ ወታደራዊ ኃይል ጋር ለመፋለም ቦታ ቦታቸዉን ሲይዙ ጥይት በላያቸዉ ዘነበባቸዉ ።

የተኩስ ልዉዉጡ አይሎ ቀጠለ ። ጌታቸዉ ጥሩነህም ቦታ እየቀያየረ ከፊት ለፊታቸዉ መሽገዉ ከሚታኮሱት ወታደሮች አብዛኛዎቹን ጣለ ። ከራሱ ወገን ጥላሁንና ተካ (ዘጋምባ) ተመትተዉ ሲወድቁ የተመለከተዉ ጌታቸዉ ፤ አጸደወይን ሰቡንና ጌታቸዉ የኋላሸትን እንዲያመልጡ ነገራቸዉ ። ለዚህም በሽፋን እየተታኮሰ ሲከላከልላቸዉ ቆየ ። በዚህ መሀከል ፤ ግራኙ ጌታቸዉ ግራ እጁን በመመታቱ እንደልቡ መታኮስ አልቻለም ።ሁኔታዉን በማስተዋሉ፤ የትግል ጓዱን በዚያ መሰሉ ቅጽበት ዉስጥ ጥሎ ለማምለጥ ያልፈቀደዉን ሞክሼዉን (ጌታቸዉ የኋላሸትን) እንዲያመልጥ ጎተጎተዉ ። እርሱ ግን ማምለጥ ካልቻለ እጁን እንደማይሰጥና ራሱን እንደሚያጠፋ ወስኖ ነበር ። እናም በፍጻሜዉ ሰዓት የቀረችዉን አንዲት ጥይት የጎረሰዉን መሣሪያ አፈሙዝ ወደገዛ ራሱ በማለም መተኮሻ ቃታዉን ሳበዉ ።....፣ ወዲያዉኑም ፤ሁሉም ነገር ጸጥ-ረጭ አለ። ስሙ ሲጠራ ጠላት የሚያሸብረዉ የኢሕአፓዉ ተወርዋሪ ተጋዳይ ጌታቸዉ ጥሩነህ ፤ ለትግሉ በወደቁቱ አያሌ የኢሕአፓ ቆፍጣና ጀግኖች ፈለግ ከጠላቶቹ ሲተናነቅ ወደቀ፤-ለታላቁ ዓላማዉም ተሰዋ ። **ክብር ሞቱ ለሰማዕት ።**

በሥፍራዉ የነበሩት ወታደሮች የጌታቸዉ ጥሩነህን ሞት ለደርግ ጽ/ቤት በሬድዮ አስታወቁ ። ደርጎችም ሁነቱን ታላቅ ግዳይ አድርገዉ በመቁጠራቸዉ አስከሬኑን ወደ ቤተ መንግሥት አስወሰዱትና በሬዲዮአቸዉም መረሸኑን አስነገሩ ። በቁም ሳለ መዉጫ መግቢያ ያሳጣቸዉን ሳተና በሞቱ አዩት ።ጌታቸዉ የኋላሸት ከሞት ቀለበት አምልጦ ከጊዜ በኋላ ይህን ታሪክ ለማስጻፍ በቃ ። አጸደወይን ደግሞ ካመለጠች በኋላ የወርቅ ሀብሏን ተቀብለዉ ቤታቸዉ ዉስጥ በሸሸጓት አንዲት ሴት ጠቋሚነት ተይዛ ፊቷ በሳንጃ ተዘልዝሏል ።

የጌታቸዉ ጥሩነህ ትንሽ እህት ወንድሟ በተሰዋበት ዕለት በአረመኔዉ ቀልቤሳ ነገዎ በሚመራ አሳሽ ቡድን ከቤቱ ተወስዳ ከመሰቃየቷም በላይ ለረዢም ጊዜ ታስራ ቆይታለች ። ወላጅ እናቱ ከሔዱበት የኤርትራ ዘመቻ ሲመለሱ የተቀበላቸዉ በቀበሌ የታሸገ ቤት ነበር ።

ይህን ስንል ከአጼ ቴድሮስ ውጪ የሳችውን ታሪክ ማንም ሊጽፍ አይችልም ወይም አይገባውም ለማለት አይደለም ። ታሪክን ለመጻፍ ግን ታሪክን ማወቅ ያስፈልጋል። ወያኔ ለስልጣን ከበቃ ጀምሮ የኢሕአፓን ታሪክ በቅጥረኞቹ ማጻፍን ተያይዞታል ። በሬው ደግሞ በዚህ መስክ ወላድ ነው ። ሌሎች ደግሞ ነበርነ ፤ ምስክርነት፤ የደም ምናምንቴ ፤ ወዘተ በሚሉ ርእሶች በተጻፉ መጣጥፎች ብዙ ቀበጣጥረዋል ። በድርጅቱ ኣልፈናል ብለው ደግሞ ገና የነበሩ ሞተው ሳያልቁ አስር በመቶ ሀቅን በ90 በመቶ ውሸት እያጅቡ ጣጥፈዋል ። ታሪክ የተማሩና እያስተማሩ ያሉ ሁለት ዶክተሮች (ሁለቱም ለአጭር ጊዜ በድርጅቱ አልፈዋል) በበኩላቸው ስለ ቀይ ሽብር አሳዝኝ ትረካ አቅርበዋል ። ርዕሳችን አለምክንያት አይደለም ።

በኢሕአፓ ላይ የተረጨትን ሀሰቶች ሁሉ ተከታትሎ ማጋላጡ ራሱን የቻለ ቀጣይ ስራ ሆኗል ። ዘመቻው የተጀመረው በአረመኔው ደርግ ሲሆን ወያኔና ሻዕቢያም እውነት ነው በሬውም ወልዷል፤ ጥጃዋም ወተት እየሰጠች ነው በሚል ደረጃ ለዓመታት አጅበውታል፤ ዋሽተዋል ። ዛሬ መጽሀፍ ጻፍን ብለው የተሰየሙት እንደሚሉት ሁሉ ድርጅቱ ለወያኔና ሻዕቢያ ፍራሽ ሆኖላቸው በነበር ከምስረታቸው ጀምሮ ባላጠቁት ባልዘመቱበት ነበር ። ዋሾዎቹ ግን ቼ ብለው ሀሰትን ሊጋልቡ ሲነሱ ይህን ዓይነቱን ጥያቄ ማንሳት አይፈልጉም ። የቀይ ሽብርን ዓይን ያወጣ ጸረ ሕዝብ ወንጀልን በጠራራ ጸሐይ ይክዳሉ ። የነበሩት ስርዓቶች ያበላሹትንና ሀገርን የጎዱበትን ሀቅ ክደው ጥፋቱን ሁሉ በኢሕአፓ ላይ ለመጫን ይጥራሉ ። የኤርትራን ጉዳይ እንደ ምሳሌ ብንውስድ በንጉሱ ጊዜ ፖለቲካው የተበላሸ ሲሆን በደርግ ዘመን ደግሞ ሁለንተናው ብልሽትሽት ብሎ እንገንጠል ላሉት አመችቷል። ለሻዕቢያ የትግራይ ወጣቶችን የገበሩት ዛሬ ሀፍረተ ቢስ ሆንው የሚተረተሩት እነ ስብሐት ነጋ ናችው ። በ1983ም በርቱ ተገንጥሉ ብለው የቧረቁት ወያኔዎች መሆናቸውን ሕዝብ ያውቃል ። ለዚህም ነው የአብዬን ለእምዬ ልክኩ ቅጥፈት ሆኖ የተጋለጠው ። ኢሕአፓ ሳይመሰረት (የተመሰረተው በኤርትራ ትግል ከተጀመረ በኋላ ቆይቶ ነውና) ለተጀመረ የግንጠላ ሂደትና ድርጅት ኢሕአፓ ተጠያቂ ሊሆን አይችልም"። በሀገራችን የነበረውን ጭቆናና የሙብት ረገጣ ተቃውሞ ሙብት ይከበር፤ ዴሞክራሲ ይስፈን ባለም ኢሕአፓን በግንጥላ መክሰሱ ከሀቅ የተጣላ ነው ።

ሐሰት ሲደጋገም ሀቅ ይሆናል ወይም ይመስላል በሚለው የናዚ ፈሊጥ ደርግና ወያኔ ውሸታቸውን በመደጋገም ሀቅን ፈልጎ ማግኘት የማይፈልጉትን ለማወናበድ ችለዋል ። በዚህ መስክ ዛሬም አርጅቶ እያለ ነጋ ጠባ የሚዋሸው ጸረ ኢትዮጵያው ወልደስላሴ (ስብሐት) ነጋ ምሳሌ ነው ። ዚያድ ባሬ ኦጋዴንን ሲወር እንዋጋው ብለን ነበር ያለው አንድ ምሳሌ ነው ። ወያኔ በሞቃዲሾ ቢሮ ከፍቶና ሲሶ ኢትዮጵያ የሶማሌ መሬት ነው ብሎ በፊርማ አጽድቆ ጸረ ኢትዮጵያ ጸረ አማራ ነኝ ከሚለው ዚያድ ባሬ ጋር የተባበረውን ሕዝብ ኣያውቅም ብሎ ይዋሻል ።

አረመኔው ደርግ በበኩሉ በወቅቱ የፖለቲካ ትግል ኢሕኣፓ እያሸነፈው ነበርና የሶማሌ ወረራ ከስማይ የወደቀ መና ሆኖለት ሀገርን መከላከል በሚል ሽፋን ሁለት ወፍ ባንድ ድንጋይ ገድሏል።

# ነጻ ሀሳብ

## የኢሕአፓን ታሪክ መጻፍ የሚችለው ኢሕአፓ ብቻ ነው

ኢሕአፓ ለዚያድ ባሬ ድጋፍ ሰጥቷል በሚልም ወታደሩንና ሕዝቡንም ቀሰቀሷል፤ ኢሕአፓንም ለማጥቃት ተጠቅሞበታል ። ይህንን ጭፍን ውሸት ዛሬም የሚያራግቡ አሉ ። ኢሕአፓ ዚያድ ባሬን ደግፎ በነበር ስደተኞቹ በሶማሊያ መከራን ባልተቀበሉ ነበር ። ዚያድ ባሬ እንደፈለገውም --ወያኔ እንዳደረገውም-- የኢትዮጵያ መሬት የሶማሊያ ነው ባለም ነበር ። መሰል ውሸቶች በዘመናዊ ፍራሽ አዳሾች እየታደሱ ቅርስ ይመስል ከትውልድ ትውልድ ይተላላፋሉ ። ብልሽቱ መረን በመልቀቁም ሕዝብን የፈጀው መንግስቱ ሳይቀር ከተሰደደበት ሆኖ የበኩሉን በመጽሐፍ መልክ ሞክሮ ነበር ።

ኣንደኛውን ታሪክ ጻፍኩ ባይ በተመለከተ እውነቱ አበራ " የግለሰብ ስንክሳር እንደታሪክ" ብሎ በመስታወት መጽሔት ጥቅምት-ህዳር 1986 ያሰፈረውን መጥቀስ ተገቢ ይሆናል ፤ታሪክ ጸሀፊዎች በየዓይነቱ ናቸው። ታዋቂው የፈረንጅ ታሪክ ጸሐፊ አርኖልድ ቶይንቢ ለምሳሌ ጥቁር ሕዝብ ለዓለም ስልጣኔ ምንም አላበረከተም ብሎ ከአክሱም እስከ ሶንጋይ ና ቲምቡክቱ ወዘተ የነበረውን የአፍሪካ ታሪክ በዘረኝነት ክዷል ። ለሌሎች ታሪክ ተረት ነው ። ለኣንዳንዶች ለም አንጎል የሚያፈልቀው ፈጠራ ነው ። አሉባልታም እንደታሪክ ሲውገረገር ቆይቷል ። በታሪክ ሽፋንም ጀግና ነበርኩ ብሎ ኢምንትነትን፤ባንዳነትን ለመደበቅ ጥረት ይካሄዳል ።

ታሪክ ሲጻፍ ሁሌም ሀቅ ነው ማለት አይቻልም ። ብዙዉን ጊዜ ኣይደለም ብንል ምናልባትም ትክክል ይሆን ይሆናል ። ታሪክ ጸሀፊዎች ለገዢዎች ሰግደው ጻፉ የተባሉትን እንደሚጽፉ ሩቅ ሳንሄድ የመጨረሻውን አጼ በማወደስ ፣ አጼ ቴድሮስን በማንቋሸሽ ይጻፉ የነበሩትን ማስታወሱ ይበቃል ። ወያኔ ለስልጣን ሲበቃም ተራራውን ያንጠቀጡ ጀግኖች ብሎ የሚጽፍ የብዕር ባሪያ ገዝተው ተጥቅመውበታል። ስለ ስዩም መስፍን ጀግንነትስ መጽሐፍ አልተከተበም ? በአጭሩ ታሪክ ተራኪዎችም ይገዛሉ ። በረከት ሀብተስላሴ ፤ ገብሩ ታረቀኝ ፣ ኢብሳ ጉተማ ፤ ወዘተ ሀሰትን ሀቅ ብለው ታሪክ ብለው ጸሐፊዎች ናቸው ። ታሪክን ለመጻፍ ኣንድም ታሪኩን በስማ በለው ሳይሆን በጥልቀት ማወቅ የሚያስፈልግ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የራስን ስሜት፤ መሰረተ ቢስ ግምትና ጥላቻ በታሪክ ሽፋን ማስፈር ማስተጋባት አይገባም ። ስለ ኢሕኣፓ ለቀጣዩ ትውልድ ይድረስ መጽሐፍ የጻፈው ለምሳሌ ራሱን አዋቂና ዋና አድርጎ ለማቅረብ በመነሳት የጻፈው ተራ ተረት ሆኖ በጊዜው በሰፊው ተተችቶበታል ። ያ ትውልድ በሚል የጻፈውም ለተወሰነ ጊዜ በድርጅቱ ተሳትፎ የነበረው ቢሆንም የማያውቀውን ሀቅ ለማጣራት የፖለቲካ ጥላቻው ስላገደው የተሟላና ከተጭባጭ ስህትተቶች የራቀ መጽሐፍ ለመጻፍ አልቻለም። ልፋት ከን ቱ እንዲሉ!

ኣንደኛውን ታሪክ ጻፍኩ ባይ በተመለከተ እውነቱ አበራ " የግለሰብ ስንክሳር እንደታሪክ" ብሎ በመስታወት መጽሔት ጥቅምት-ህዳር 1986 ያሰፈረውን መጥቀስ ተገቢ ይሆናል ፤

ታሪክ ጸሀፊዎች በየዓይነቱ ናቸው። ታዋቂው የፈረንጅ ታሪክ ጸሐፊ አርኖልድ ቶይንቢ ለምሳሌ ጥቁር ሕዝብ ለዓለም ስልጣኔ ምንም አላበረከተም ብሎ ከአክሱም እስከ ሶንጋይ ና ቲምቡክቱ ወዘተ የነበረውን የአፍሪካ ታሪክ በዘረኝነት ክዷል ። ለሌሎች ታሪክ ተረት ነው ። ለኣንዳንዶች ለም አንጎል የሚያፈልቀው ፈጠራ ነው ። አሉባልታም እንደታሪክ ሲውገረገር ቆይቷል ። በታሪክ ሽፋንም ጀግና ነበርኩ ብሎ ኢምንትነትን፤ባንዳነትን ለመደበቅ ጥረት ይካሄዳል ።

የልብ ወለድ ጸሐፊ በራሱ ፈጠራ የፈለገውን ቢያሰፍር ልብወለድ ነውና አያስገርምም። የማይመስል ታሪክ ከሆነ ደግሞ በሳይንስ በፋንታሲ ልብወለድነት ተፈርጆ ሊታለፍ ይችላል ። ታሪክ ግን ሌላ ነው ። መረጃ ይጠይቃል ። ሀቅን መሰረት ማድረግ ይጠበቅበታል ። ሁለገብነት ሊኖረው ያስፈልጋል ። ታሪክ ከተለመደው የወያኔ እና ሻዕቢያ ተረት ተረት ተለይቶ ለሕዝብ የሚቀርብ፤ ሕዝብ የኖረውንና ያሳለፈውን አጠናቅሮ የሚዘግብ እስከሆነ ድረስ በ "ታሪከኛው" የግል እይታ፤ ስሜትና ቁርሾ ተጭኖ ሀቅን አርግፎ ሽምጥ ሊጋልብ አይችልም ።"

ይህን ካለ በኋላ ሐያሲው ተረት ተረት ያለውን መጽሐፍ ዋጋውን ይሰጠዋል። ገንቢ ሂስ ያርቃል ፤ ያስተምራልናም ነው ። አዋቂ አይጥፋ ያስኛል ። ሰሞነኞቹ ደግሞ ስለታሪኩም የሚያውቁት ውሱን ከመሆኑ ሌላ መሰረተ ቢስም ነው የሚጽፉት በአብዛኛው ። ለምሳሌ ምስክርነት በሚል የቀይ ሽብር ወንጀልኛ ሻምበል የጻፈውን ሆነ የወያኔን አድናቂ መጽሐፎች ገዥ ራሱ ወያኔ ነው። እነዚህን ለሙተችት መነሳቱ ብዙም ዋጋ የለውም ። መጀመሪያና መጨረሻ የሚኖረው ኣይደለምና ። ድርጅቱ ግን ሳይሰለች ለማስረዳትና ሀቁንም ለማስረገጥ ሲጥር ቆይቷል ። ለደርግም ለወያኔም ምላሽን ደግሞ ደጋግሞ ሰጥቷል ። ዘመቻው ግን አላቆመም ፤ የሚጠበቅም ነው ። ኢሕአፓ ጠላታቸው ነውና ። የድርጅቱ ታሪክ ዘርፈ ብዙና ሰፊም ነው ። ብዙሃን የተሳተፉበትና ለኢትዮጵያም ደሙን ያፈሰሰ ድርጅት ነውና። አንድ ግለሰብ የሚጽፈው ታሪክ አይደለም ። ለኢሕ አፓ ምስረታ ምክንያት የሆነው ተጨባጭ ሁኔታ ራሱ ብዙ መጽሀፍ የሚወጣው ነው ። ኢሕኣፓ 1964 ተመስርቶ ቀይ ሽብር ሲመጣበት አላከተመም ። የኢሕኣፓ ጦር ኢሕአሠም በወያኔና በሻዕቢያ በአሲምባ ሲጠቃ ትግሉ አላበቃም ። በስራዊቱ ብተና ሲመጣብትም ትግሉን ቀጠለ እንጂ ኣላቆመም ።ወያኔ፤ሻዕቢያና ሱዳንም በ 1983 ሲውጉት አልጠፋም። እስከዛሬ አለሁ ብሎ ታገለ እንጂ ። ሰፊ ታሪክ ። ይህን ሁሉ የማያውቁ ወይም በየፌርማታው የተንጠባጠቡ ደግሞ ቁንጽል ዕውቀታቸውን ታሪክ ሊሉ፣ ቢሉ አጥጋቢ ኣይሆንም አልሆነምም። የኢሕኣፓን ታሪክ ሊጽፍ የሚችለው ኢሕአፓ ብቻ ነው ሲባል ይህን ሁሉ በመገንዘብ ነው ። ቀጣይና ሰፊ ታሪክ ነውና የጋራ ጥረትንና አፍቅሮ ድርጅትንም ይጠይቃል ። በአንጻነትና በአፍራሽነት የተሰማሩ ይህን ግዳጅ በቀናነት፣ በገንቢ መንፈስና ይዘት ሊያሟሉት ኣልቻሉም፤ አይችሉምም ። ቁርሾአቸውና ጥላቻችው ያወራቸው ወይም ያጣመማቸው ናቸውና ታሪክን የራስ ቂም መወጫ ያድርጉታል ። ያያነውና የታዘብነው ነው ። በወያኔ ግፊትና ጥላ ስር በኢሕኣፓ ላይ እየውጡ ያሉት መጽሐፎች አብዛኞቹ ጎዶሎና የውሸትም ቋቶች ናቸው ። ቆንጂት ብርሃኔ ልብወለድ ብላ የጻፈችው ምርኮኛ ታሪክ ያሉትን ብዙዎቹን ይዘርራቸዋል ። ቀሪው እንግዲህ ራሱ ኢሕአፓ ሳይውል ሳያድርና ጊዜ እያለፈ ሳይጎዳ ታሪኩን መጻፉ ነው ። አደራ እንላለን ። ምስክሮቹና ታሪክ ሰሪዎቹ ሳይለዩን ። እስከዚያው ግን ለሀሰተኞቹ ምላሽ መስጠቱ በልክም ቢሆን መቀጠል ኣለበት ።

## መድረክ በዋሽንግተን ከፍተኛ ተቃውሞ ገጠመው

ከ ገጽ 3 የዞረ

በ10/7/2012 (እኤአ) መድረክ በዋሽንግተን ዲሲ ባዘጋጀው ስብሰባ ላይ፣ በዕለቱ ለተሰብሳቢው ንግግር ካደረጉት አራት የመድረክ አባላት መካከል አቶ ስዬ አብርሃ ከፍተኛ ተቃውሞ ገጠመው:: የቀድሞው የወያኔ የመከላከያ ሚኒስቴር የነበረው አቶ ስዬ አብርሃ፣ንግግር ለማድረግ በተነሳበት ወቅት፣ የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ደርጅት አባላት የሆኑት ወጣቶች፣ "አንተ ስለፍትህ ልታስተምረን አትችልም" በማለት ንግግሩን እንዲያቋርጥ አስገድደውት ነበር::ይሁንና የስብሰባው መሪ የነበረው ግለሰብ የወጣቶቹን የመናገር እና የመቃወም መብት በመጣስ፣ «ይህ የሰለቸ ፖለቲካ ነው፤ ሴኩሪቲ ጥራ፤ አስወጣልኝ»...በማለት ወጣቶቹን ለማስቆም ቢሞክርም ባዳራሹ ከነበሩት ተሰብሳቢዎች መሀል ብዙዎቹ ፣ "የመናገር መብት አላቸው፤ ልትከለክላቸው አትችልም" በማለታቸው በሁለቱ ወገን የነበረው ፍጥጫ ሊረግብ ችሏል::

ከዚህ በኋላ በጥያቄና መልስ ጊዜ የኢወክንድ ወጣቶችን ጨምሮ ሌሎች ወገኖችም ጥያቄዎቻቸውን ለአቶ ስዬና ለሌሎችም አቅርበዋል:: ድምጻዊ ጠለላ ከበደ በተሰጣት ሁለት ደቂቃ ውስጥ የነበራትን በርካታ ጥያቄዎች ለመጠየቅ ጊዜ ባይኖራትም ፣ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ተከሰው ፍርድ ቤት በቀረቡበት ዘመን፣ የፍርድ ሂደቱን ለመከታተል በተገኘችበት ወቅት የወያኔ የጸጠታ ሠራተኞች አፍሰው ሰንዳፋ እስር ቤት ውስጥ አስገብተው ጸጉራቸውን በተመሳሳይ ምላጭ ከተላጩት 500 ሰዎች መሀል አንዷ እንደነበረች እና ይህን ድርጊት የፈጸምከውም አንተ ሰዬ አበረሃ ነበርክ በማለት ከነገረችው በኋላ፣ አንተም እኔም ፍትህ ባለበት አገር አሜሪካ በመገናኘታችን እግዚአብሔር ይመስገን ወደፊትም ፍትህ ሲመጣ አገር ቤት ለመገናኘት ያብቃን ስትል ሕዝቡ ድጋፉን በጭብጨባ ገልጿል:: "የማረካችኋቸውን የኢሕአፓ ታጋዮች የት አደረሳችኋቸው ተብሎ በ ኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት አባላት ለቀረበው ጥያቄ ከመድረክ መሪዎችም ሆነ ከአጋፋሪ ባንዳዎቻቸው የተሰጠው ምላሽ በእብሪትና በፌዝ የተመላ ነበር። በቀይ ሽብር መስዋእት በሆኑ ጓዶቻችን አጽም መነገድ የለመደው ወያኔ ዛሬም ለሰው ሕይወት ያለውን ደንታ ቢስነት የሂሳብ ማወራረድ ጊዜው ገና ነውና እንደዚህ አይነት ጥያቄ አታቅርቡ ነበር መልሱ። ድሮስ ከገዳይ ምን ይጠበቃል።
ሌላው አስገራሚ ተናጋሪ "ፕሮፌሰር" መራራ ትግሉ ዳር የሚደርሰው የወያኔ ወንጀለኞች የተቃውሞ ትግሉን ሲመሩት መሆኑን "ምሳሌ" እየጠቀሱ ሊሰብኩ ሞክረዋል ካሉ በኋላ ይች ናት ትምህርት!" ሲሉ የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት አባላት "ለገዳዩ ወያኔና ለአሽቃባጭ ባንዳዎች ያላቸውን የአይበገሬነት መንፈስና ትግሉን ዳር ለማድረስ ያላቸውን ቁርጠኝነት" ገልጸውልኛል።
በመጨረሻም፣የመድረኩ መሪ የነበረው "ዶ/ር" ካሳ የተባለው ሰው የሰለቸ ፖለቲካ ነው ሲል የተናገረው አረፍተ ነገር ብዙዎቹን ያሳዘነና ያስገረመ አባባል ሆኖ ተገኝቷል:: አንዳንድ ግለሰቦች የፍትህ ጥያቄ ይሰለቻል ወይ? እንደዛ ከሆነ በ 1997 ምርጫ ስለሞቱት ንጹሀን ዜጎች መጠየቅ የሰለቸ ፖለቲካ ነው? መቼስ ቢሆን ሊባል ይችላል? ሲሉ አንዳንዶቹ ደግሞ፣ጥያቄው የቀረበው ለአቶ ስየ ሆኖ ሳለ ይህ ግለሰብ መልስ ሰጪ ማን አደረገው? ሲሉ ተደምጠዋል። ይህንኑ በተመለከተ ያገኘነውን ግጥም ልናስነብባችሁ እንወዳለን።**"ከእባብ እንቁላል እርግብ አልተፈጥሮም፣ ግፍን በማራዘም ነጻ እገር አልታይቶም።"::**

ከእባብ እንቁላል እርግብ አልተፈጥሮም፣
ግፍን በማራዘም ነጻ እገር አልታይቶም።
እነህ ወያኔዎች አዲስ ካባ ለብሰው፣
ፕሮፌሰር ዶክተር ምሁር አቀናጅተው፣
አሸርጎጅ አጎንባሽ መርጠው እስከትለው፣
ስልጡን እደርባዮች ከመሃል በትነው፣
እባብ እርግብ ሊወልድ፣
በሬው ካራጅ ሊለምድ፣
ስብሰባ ተጠርቶ፣
ወገን ሰምቶ መጥቶ፣
ከእምነት እዳራሽ ገብተን ተቀምጠን፣
በዚህ በእሜሪካ ከሰአት እሁድ ቀን፣
እየ ግዜ ደጉ ጉድ ሰማን ጉድ እየን።
"እርባ እመት በሙሉ ሰምተን ሰልችቶናል፣
የሙብትን ጥያቄ ማንሳት ምን ይረባል?"
ብለው መከሩነ፣
መንበርከክ መገዛት ይሻላል አሉነ።
ከዛም አጠገቡን በሰፊ ዲስኩር፣
"ምንም ጉርሻ ቢሸጥ በአራት ብር፣
ልማቱ ቀጣይ ነው በጦብያ ምድር።"
አሉን አትቸኩሉ ተረጋጉ እናንተ፣
ለምን ታዝናላችሁ ወገን ስለሞተ
በኃላ ይደርሳል ሂሳብ ማወራረድ
አሁን መቀጠል ነው በህዋት መንገድ
ላዲሱ ተሸዋሚ ጊዜ ስጡት ፋታ
ግፍን እንዲቀጥል በመለሰ ፈንታ
ትግል ለምናችሁ ብለው መከሩነ
ታሪክን አጣቅሰው እያስተማሩነ
**"የአንባገነን ስራት ገዳይ መኮንኖች**
**ሊሆኑ ይገባል ተቃውሞን መሪዎች"**
ሊቢያን ጋዳፊን መመልከት ነው አሉ
እኝህ **"ታላቅ ምሁር"** በጣም ያስተዋሉ
ታሪክን ሲጽፉ እንደሚያመቻቸው
እንደምን ይጥማል ግሩም ድለላቸው?
በትረ ስልጣን ይዘው ከማዶ ቢገሉን
በዘር ቢለያዩን
አስረው ቢያሰቃዩን
ቢያፍኑን ቢወግሩን
ሰንደቅን ቢደፍሩም
እምዬን ሀገሬን ኢትዮጵያን ቢያፈርሱም
በእምነት ጣልቃ ገብተው ሀገሩን ቢያምሱት
የጦር ሀይላችንን የቡድን ቢያረጉት
የሀገራችንን ሀብት የህዋኣት ቢሉት
ከቶ ምን እዳቸው
እኝህ "ታማኝ ምሁር" እንደአባባላቸው
ኢትዮጵያ ጀግና የላት ስዬ አንበሳቸው
ለድል የሚያበቃን መርቶ መድረካቸው
ትህምርቱ ቀጠለ
እንዲህም ተባልነ
"እኛ አስገንጥለናት ሌላ ሀገር ብትሆንም
አሰብ ከኤርትራ መለየቶ አይቀርም
የለም አትቸኩሉ ቀዝቀዝ ስከን በሉ
ምን አስቸኮላችሁ
"መታኮስ መጋደል ጦርነት ካሻሻችሁ
**ወያኔ ከጀርባ ሻቢያ ከፊታችሁ**
**እናንት እንዳቻምናው ከመሃል ሆናችሁ**
**ሁሌም ዝግጁ ነን ልንጨርሳችሁ"**
ብለው አጽናኑነ አይዝዋችሁ አይዝዋችሁ
ይህማ መሆኑ እኛ መች ጠፍቶነ
ከረምን ሰነበትን ብዙ ዘመን ሆነ
የወያኔን ተንኮል ከሰማን ካየነ
**ከእባብ እንቁላል እርግብ አልተፈጥሮም!**
**ግፍን በማራዘም ነጻ ሐገር አልታይቶም!**
**ሰማነ ስማነ አደመጥነ በጣም**
**እምቢኝ! አልነ እንጅ ከባንዳ አንጣጣም**
**የተገደልን እኛ ሕዝባችንን ያልነው!**
**የታሰርን እኛ መብታችንን ያልነው!**
**የተጠቃን እኛ ለአንድነት ያበርነው!**
**የተጋዝን እኛ ኢትዮጵያን ያልነው!**
ይህ የገንጣይ አሽከር
ይህ ገዳይ አምላኩ
ክብር ለሱ ምኑ ነው?
ሐገር አስገንጣዩ ሰንደቅ አቃጣዩ
ወገኑን አራጁ ሕዝብን ከፋፋዩ
ህውአት መሪው ነው!
**ሐገር ከፋሺስትም ከጠባብ ይበልጣል!**
**ተዋርዶ ከመኖር መሞት ይመረጣል!**
**በዘር ከመራራቅ አንድነት ይሻላል!**
**ከድርጅት አጥር ነጻነት ይጠብቃል!**
**በእብሪት ተወጥሮ ግፍን ከማራዘም!**
**ደንታ ቢስ ከመሆን ለወገናችን ደም!**
**ጥርት ባለ መስመር ለትግል እንትመም!**

**ከእንግዲህስ ይብቃ በቁም መሞት ይቅር**
**እንደ እሳት የፈሩት ያብብ ያገር ፍቅር!**
**ኢትዮጵያዊነት ማእበል ይሁንና!**
**የጎበዝ አለቆች ይውለድ ብዙ ጀግና!**
**የምን ግዜ ስጡት ሂሳብ ያወራርድ!**
**ዞሮ መግቢያችንን እትዮጵያን ሲንድ!**

**ወያኔማ ሁሌም ወያኔ ነው!!!**
**አእስቀድሞ መግታት ቡከኑን ባንዳ ነው**
**ተቃዋሚ መስሎ ለገንጣይ የሚያድረው**
**የቁርጥ ቀኑ ግዜ የሚብረከረከው**
**ሂሳብ ማወራረድ ብሎ የሚዘምረው**

**ተጋግሎ ይንደድ ኢትዮጵያዊው ቀመር**
**በአንድ ሆነን እናምጽ ሳንከፈል በዘር**
**ከሀገር እንዲወገድ ግፍና መከራ**
**ግዳጅ ከተሰጠን ሆኖ የኛ ተራ**
**ሆ ብለን ተነስትን ኑ ታሪክ እንስራ!**
**ኢትዮጵይ እናታችን ዛሬም በኛ ትኩራ!!**

## ተነስ ተነስ!!
## አትነሳም ወይ?
## የግፍ አገዛዝ አይበቃሕም ወይ!!




## የአምነት ነጻነታችንን ለማስከበር ትክሻ ለትክሻ ተደጋግፈን በጽናት ቆመናል!!
## ፈጣሪን የሚያሸንፍ የለም!




## አንድ ነን!
## የዘረኞች ሴራ የማይለየን!




## እንቢ ለወያኔ!! እንቢ ለባንዳ!!




